የሰብለ ደግሞ ተደፋፍቷል:: “ምነው! ምነው! ግርማ?” አሉት:: “እማዬ ስላልጠገብኩ ነው” አለ:: “ካልጠገብክ ጨምሩልኝ አትልም?” ግርማም፣ “እማ፣ ሁለተኛ አይለምደኝም፤ ለዛሬ ይቅር በይኝ” አላቸው:: እናታቸውም፣ “አዎ፣ መዋሸትና የሰውን ገንዘብ መቀማት ጥሩ ያልሆነ ስነምግባር ነው” በማለት መከሩት::

## 2ኛ ቀን


### አንብቦ መረዳት

ጥያቄዎችን በምንባቡ መሠረት በፅሁፍ መልሱ::

1. ሰብለና ግርማ የተጣሉት በምን ምክንያት ነው?
2. ጥፋት ያጠፋው ማን ነው?
3. እናቱ ግርማን ምን ብለው መከሩት?

### ቃላት

በተገቢ ቃላት ሠንጠረዡን አሟሉ::




1. ህግ ማክበር
2. እናት ማክበር
3. ____________
4. ____________
5. ____________

### መፃፍ

ዓረፍተነገር ሥሩ::

1. ንብረት 2. ሥነሥርዓት 3. ሥነምግባር 4. ማክበር

## 3ኛ ቀን

### ማዳመጥ

## ሃላፊነትን መቀበል

### ቃላት

ቃላትን በማቃረን አዛምዳችሁ ፃፉ

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 1. መብላት | ሀ. መዘግየት |
| 2. መፍጠን | ለ. መጀመር |
| 3. መጥፎነት | ሐ. ጥሩነት |
| 4. መጨረስ | መ መጠጣት |

### ማጣመር

ሀ. የተጓደሉ ፊደላትን በመፃፍ ቃላት መስርቱ።

1. አከ _ _ 2. ተንከባ _ _ 3. ሥነምግ _ _ 4. መም _ _

ለ. ቃሉን ከቅጥያው ጋር (-ነት) በማጣመር ሌላ ቃል መስርቱ።

ምሳሌ፦ ክፉ + ነት → ክፉነት

ሀ. ታማኝ ለ. ደግ ሐ. ቅን መ. የዋህ ሠ. ብልህ

### ግለንባብ

## የጊዜ አጠቃቀም



ማንኛውም ሰው ጊዜውን በአግባቡ መጠቀም ይኖርበታል። በዚህም መሠረት ተማሪዎች የትምህርት ቀናትንና የበዓል ቀናትን በመለየት ጊዜያቸውን ከፋፍለው ይጠቀማሉ። ተማሪዎች በየሣምንቱ የዕረፍት ቀን ጊዜያቸውን ከፋፍለው ለመጠቀም ዕቅድ ቢያወጡ ጥሩ ነው። ለምሳሌ ቅዳሜ እስከጧቱ 2:00 ድረስ ልብሳቸውን ለባብሰው ቁርሳቸውን ይበላሉ።

★★★ተማሪዎች ቁርሳቸውን ከበሉ በኋላ ምን ያደርጋሉ ብላችሁ ታስባላችሁ?"★★★

ከ2፡00 እስከ6፡00 የማጠናከሪያ ትምህርት ይማራሉ፡፡ ከ6፡30 እስከ 7፡30 ምሳቸውን ይበላሉ፡፡ ከ7፡30 እስከ9፡00 ያርፋሉ፤ ከ9፡00 እስከ 10፡00 ይጫወታሉ፤ ከ10፡00 እስከ12፡00 ወላጆቻቸውን በሥራ ያግዛሉ፤ ከምሽቱ 12፡00 እስከ2፡00 የቤት ሥራቸውን ይሠራሉ፤ ያጠናሉ፡፡ በዚህ መሠረት ያወጡትን ዕቅድ በተገቢ መንገድ የሚጠቀሙ ተማሪዎች መልካም ሥነምግባርን ያዳብራሉ፤ ውጤታቸውም ከፍተኛ ይሆናል፡፡

## 4ኛ ቀን

### አንብቦ መረዳት

**ለጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልስ ስጡ፡፡**

1. ተማሪዎች ምሳቸውን የሚበሉት ከስንት እስከስንት ሰዓት ነው?
2. ወላጆቻቸውንስ የሚረዱት ከስንት እስከስንት ሰዓት ነው?
3. የሚጫወቱትስ ከስንት እስከስንት ሰዓት ነው?

### ቃላት

**ለጥያቄው ተገቢ ምላሽ በቃላችሁ ስጡ፡፡**

በቀን ውስጥ ስንት የምግብ ጊዜያት አሏችሁ? ስማቸውን ግለፁ፡፡

### መፃፍ


**የሰኞ የሥራ እቅዳችሁን በተሰጠው ጊዜ መሠረት ፃፉ፡፡**

| የሰኞ ተግባራት | የተሰጠ ጊዜ |
|---|---|
| ፊቴን ታጥቤ ቁርሴን እበላለሁ፡፡ | ከ1፡00 - 1፡30 |
| ወደትምህርት ቤት እሄዳለሁ፡፡ | |
| እማራለሁ፡፡ | |
| ወላጆቼን እረዳለሁ፡፡ | |
| አጠናለሁ፡፡ | |

# 23ኛ ሳምንት

## 1ኛ ቀን

### ማዳመጥ



የሥርዓተፆታ እኩልነት

### ቃላት

ቃላቱን በማንበብ ትርጉማቸውን ከመምህራችሁ ጋር ተወያዩባቸው፡፡

1. የሥርዓተፆታ እኩልነት
2. እኩል ተሳትፎ
3. ፍትሀዊነት
4. እኩል የሥራ ክፍፍል

### ማጣመር

ቃሉን ከቅጥያው ጋር አጣምራችሁ ፃፉ፡፡

ምሳሌ፡- እኩል - ነት → እኩልነት

1. ወንድ-ነት 2. ሴት-ነት 3. ሰው-ነት 4. ልጅ-ነት

### ግለንባብ

#### "ወገን ለወገን"



ነጃትና ደረሰ በዓይንማዝ በሽታ ምክንያት ዓይነስውር ሆነዋል፡፡ ሁለቱም የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው፡፡ ግብረሠናይ ድርጅት እየረዳቸው በአንድ ግቢ ውስጥ ይኖራሉ፡፡ በትምህርት ቤታቸውና በቤታቸው መካከል የመኪና መንገድ አለ፡፡ ደረሰና ነጃት ወደትምህርትቤታቸው

ለመሄድ መኪና መንገዱን ማቋረጥ አለባቸው:: በዚህም የተነሳ የክፍላቸው ተማሪዎች ተወያዩ፤ የሥራ ክፍፍልም አደረጉ:: ሁሉም ተማሪዎች በየተራ እነነጃትን ይዘው ወደትምህርትቤት ይመጣሉ፤ ወደቤታቸውም ይመለሳሉ:: ስለዚህ ደረሰና ነጃት ያለምንም ስጋት ትምህርታቸውን መከታተል ቻሉ::

## 2ኛ ቀን

### አንብቦ መረዳት

ጥያቄዎችን በምንባቡ መሠረት መልሱ::

1. የክፍላቸው ተማሪዎች እነነጃትን ለመርዳት ምን አደረጉ?
2. እናንተስ እንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ቢያጋጥማችሁ ምን ታደርጋላችሁ?

### ቃላት


ዓረፍተነገር ሥሩ::

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1. እኩል | 2. ፆታ | 3. ፍትህ | 4. የሥራ ድርሻ |

### መፃፍ

ተስማሚ ቃላትን በሳጥኖች ውስጥ ፃፉ::

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| የዕድሜ | የሥራ | የባህል | የሀይማኖት | የቋንቋ | የፆታ |



# 3ኛ ቀን



## ማዳመጥ

### የሥርዓተፆታ እኩልነት

## ቃላት

ቃላቱን በማቃረን አዛምዱ።

| | | "ሀ" | | "ለ" |
|---|---|---|---|---|
| ለ | 1. | እኩልነት | ሀ. | መናቅ |
| | 2. | የበላይነት | ለ. | አድሏዊነት |
| | 3. | ማክበር | ሐ. | አንድነት |
| | 4. | ልዩነት | መ. | መጉዳት |
| | 5. | መጥቀም | ሠ. | የበታችነት |


## መነጠል

በነጠላ ቁጥር ፃፉ። ምሳሌ፦ ክበቦች → ክበብ

1. ድርጅቶች
2. አድሎዎች
3. ተጎጂዎች
4. ተጠቃሚዎች
5. ስጋቶች

## ግለንባብ

### የፍትህ ምንነት



ፍትህ ማለት አለማዳላት ማለት ነው። እውነትን መናገር ነው፤ እውነትን መሰረት አድርጎ መሥራት ነው። ፍትህ በትምህርትቤት፣ በቀበሌና በቤተሰባዊ ኑሮ ውስጥ አስፈላጊ ነው። ፍትህ የሰዎች ህይወትና ኑሮ ጥሩ እንዲሆን ያደርጋል። በሰዎች መካከል ምንም አይነት ልዩነትና አድሎ እንዳይፈጠር ይጠቅማል። በጓደኝነትም ደረጃ አንዱ የበላይ ሌላው የበታች እንዳይሆን ያግዛል። ስለዚህ ፍትህ አንዱ ተጎጂ ሌላው ተጠቃሚ እንዳይሆን በማድረግ የሰዎችን መብት ያስከብራል።

## 4ኛ ቀን

### አንብቦ መረዳት

ጥያቄዎችን በምንባቡ መሠረት መልሱ፡፡

1. እውነት መናገር ለምን ይጠቅማል?
2. ፍትህ የት የት ይከበራል?
3. ፍትህ ባይኖር ሰዎች ምን ምን ጉዳት ይደርስባቸዋል?

### ቃላት

ዓረፍተነገር ሥሩ፡፡

1. ተጠቃሚ 2. ተጎጂ 3. ተናጋሪ 4. ተቆርቋሪ

### መፃፍ

በምሳሌው መሠረት ቃላትንና ሐረጋትን መድቡ፡፡


| | |
|---|---|
| ማዳላት | መዋሸት |
| እውነት መናገር | ራስን ብቻ መጥቀም |
| ትክክለኛ ፍርድ መስጠት | ጓደኛን ማበላለጥ |
| ሁሉንም ሰው እኩል ማየት | |

| | ፍትሃዊ የሆነ | ፍትሃዊ ያልሆነ |
|---|---|---|
| ምሳሌ፦ | እውነት መናገር | ጓደኛን ማበላለጥ |

# 24ኛ ሳምንት

## 1ኛ ቀን

### ማዳመጥ



**የአካል ጉዳተኝነት**

### ቃላት

ዓረፍተነገር ሥሩ።

1. ጉዳት  2. ድጋፍ  3. ሚና  4. ህብረተሰብ

### ማጣመር


በብዙ ቁጥር ፃፉ።

ምሳሌ፡- ተማሪ → ተማሪዎች

1. ጥያቄ  2. ሥራ  3. ዜጋ  4. ሁኔታ

### ግለንባብ

#### ጎበዟ ቆንጂት



ቆንጂት ዓይነስውር ናት። የምትማረው ማየት ከሚችሉ ተማሪዎች ጋር ነው። አንድ ቀን መምህራቸው፣ “ተማሪዎች፣ ገፅ ስምንትን አውጡ” አሉ። በመቀጠል “እስኪ የመጀመሪያውን ጥያቄ መልሱ” በማለት ተናገሩ። ተማሪዎችም “እኔ፣ እኔ” እያሉ እጃቸውን አወጡ። ቆንጂትም እጇን አወጣች። ወዲያውኑ “መምህር ጥያቄው ከመመለሱ በፊት ጥያቄ አለኝ” አለቻቸው። መምህሩም በመገረም “ጥያቄው አልገባሽም እንዴ?” አሏት። ቆንጂትም “ጥያቄውን ለእኔ አላነበቡልኝም፤ ስለዚህ መሳተፍ አልችልም” አለቻቸው። መምህሩ ደነገጡ። “ይቅርታ! ያነበብኩልሽ መስሎኝ ነው።

ሁላችሁም አዳምጡኝ” በማለት ጥያቄውን ተረጋግተው አነበቡላቸው:: ከዚያም በኋላ ቆንጂት እንድትመልስ እድል ሰጧት:: በሚገባ አብራርታ መለሰች:: መምህሩም “ቆንጂት በጣም አመሰግናለሁ! ችሎታሽን ስላሳየሽን እናጨበጭብልሻለን” አሉ:: ቆንጂትም “አሁን ምቹ ሁኔታን ፈጥረውልኛል” ብላ ፈገግ አለች::

## 2ኛ ቀን

### አንብቦ መረዳት

ጥያቄዎችን በምንባቡ መሠረት በፅሁፍ መልሱ::

1. ቆንጂት ምን ዓይነት ተማሪ ናት?
2. ቆንጂት መምህሯን ምን ብላ ጠየቀቻቸው?
3. የቆንጂት መምህር የደነገጡት ለምንድን ነው?
4. በመጨረሻ መምህሩ ቆንጂትን እንዴት አበረታቷት?

### ቃላት

በቃላችሁ ዓረፍተነገር ሥሩ::


1. መፍጠር
2. መሳተፍ
3. መገረም
4. መደንገጥ
5. ማመስገን

### መፃፍ

ቃሎቹን በማጣመር ሌሎች ቃሎችን ፃፉ::

| |
|---|
| ማዕድ |
| ማረሚያ |
| መኝታ |
| ዳቦ |
| ሥጋ |
| ምግብ |

\+




| ምሳሌ፡- ማዕድ ቤት |
|---|
| |
| |
| |
| |
| |

## 3ኛ ቀን

## ማዳመጥ

### የአካል ጉዳተኝነት

**ለጥያቄው በቃላችሁ መልስ ስጡ፡፡**

የአካል ጉዳተኞች በምን በምን ስፖርታዊ ውድድሮች ሲሳተፉ አይታችኋል?

## መነጠል


**በምሳሌው መሠረት ነጥላችሁ ጻፉ፡፡**

ምሳሌ፡- ተፈጠረ → ተ - ፈጠረ

1. ተወሰደ 2. ተቀነሰ 3. ተጨመረ 4. ተገረመ

## ግለንባብ

### ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች



በየትኛውም ትምህርትቤት ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች አሉ፡፡ ከእነሱም መካከል አካል ጉዳተኞች ይገኙባቸዋል፡፡ ለምሳሌ ዓይነስውሮች፣ መስማት የተሳናቸው ወይም ሌሎች አካላዊና አእምሯዊ ጉዳት የደረሰባቸው ተማሪዎች ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡

***"አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ምቹ ሁኔታ ካልተፈጠረላቸው ምን ችግር ይፈጠርባቸዋል?"***

እነዚህ ተማሪዎች ምቹ ሁኔታ ካልተፈጠረላቸው በስተቀር በቂ እውቀት ለመገብየት ይቸገራሉ፡፡ ነገር ግን አስፈላጊ ቁሳቁስ ከተሟላላቸው ችሎታቸውን ማሳየት ይችላሉ፡፡ የትምህርት ተደራሽነትን ለማፋጠን ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች መለየትና ድጋፍ መስጠት የሁሉም ዜጋ ግዴታ ነው፡፡

## 4ኛ ቀን

## አንብቦ መረዳት

በምሳሌው መሠረት ቃላቱን መድቡ፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| ማዳላት | ማግለል | ፍቅር መስጠት | ድጋፍ ማድረግ |
| ማራቅ | ልዩነት መፍጠር | ማክበር | |

| | ለሀገር ዕድገት | |
|---|---|---|
| | የሚጠቅሙ | የማይጠቅሙ |
| ምሳሌ → | ማክበር | ማዳላት |

## ቃላት

ቃላቱን በማቃረን አዛምዱ፡፡

| | "ሀ" | | "ለ" |
|---|---|---|---|
| ለ | 1. ማክበር | ሀ. | መከልከል |
| | 2. ማግለል | ለ. | ማዋረድ |
| | 3. መጥቀም | ሐ. | ማቅረብ |
| | 4. መመረቅ | መ. | መርገም |
| | 5. መስጠት | ሠ. | መጉዳት |

## መፃፍ

በጥያቄው ላይ ተወያይታችሁ መልሱን በፅሁፍ አቅርቡ፡፡


አካል ጉዳተኞች የተለያዩ ተግባራትን እንዲያከናውኑ ምን ምን ዓይነት ድጋፎች ያስፈልጓቸዋል?

# 25ኛ ሳምንት

## 1ኛ ቀን

### ማዳመጥ

**ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎችና የሚሠሩባቸው ቁሶች**



### ቃላት

ዓረፍተነገር ሥሩ፡፡

1. ክራር  2. ዋሽንት  3. ከበሮ  4. ቃጭል

### ማጣመር

ሀ. ቃላቱን ወደብዙ ቁጥር ለውጧቸው፡፡

1. ማሲንቆ 2. ቃጭል 3. ፅናፅል 4. መለከት 5. ደወል

ለ. ፊደላቱን አጣምራችሁ ፃፉና አንብቡ፡፡

ምሳሌ፡- የ - ዋ - ን - ዛ + እ - ን - ጨ - ት → የዋንዛ እንጨት

1. የ - ጥ - ድ + እ - ን - ጨ - ት
2. የ - ዝ - ግ - ባ + እ - ን - ጨ - ት

### ግለንባብ

## ባለዋሽንቱ



አንድ ምሽት ዋሽንት ተጫዋቹ ዋሽንቱን ይዞ የባህል ሙዚቃ ወደሚጫወትበት ቤት ሄደ፡፡ ታዳሚዎቹ ፊት ለፊት ተቀምጠው የዝግጅቱን መጀመር መጠባበቅ ያዙ፡፡ የባህል ሙዚቃ ተጫዋቾቹ ወደ መድረኩ ወጡ፤ መጫዎትም ጀመሩ፡፡ ዋሽንት ተጫዋቹ መድረኩ ላይ በድንገት በመታመሙ ዋሽንቱ ከእጁ አምልጦ ወደቀ፡፡

⋆⋆⋆"ዋሽንት ተጫዋቹ የጣለው ዋሽንት ምን የሚሆን ይመስላችኋል?"⋆⋆⋆

አጠገቡ የነበረው ጓደኛውም ሳያስተውል ዋሽንቱን ረገጠው፡፡ ዋሽንት ተጫዋቹም ህመሙ ሲሻለው የዋሽንቱን መሰበር አይቶ አዘነ፡፡ ጓደኛውም "እንኳን አንተን ተሻለህ እንጂ፣ ከባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያ መሸጫ ቤት ሌላ ዋሽንት እንገዛለን" ብሎ አፅናናው፡፡

## 2ኛ ቀን

### አንብቦ መረዳት

በምንባቡ መሠረት ለጥያቄዎች ምላሽ ስጡ፡፡

1. ባለዋሽንቱ መድረክ ላይ ከወጣ በኋላ ምን አደረገ?
2. ባለዋሽንቱ ያዘነው ለምንድን ነው?
3. ጓደኛው ባለዋሽንቱን ያጽናናው ምን በማለት ነው?
4. የዋሽንት ድምፅ ስትሰሙ ምን ዓይነት ስሜት ይሰማችኋል?

### ቃላት

ባዳመጣችሁት መሠረት የባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያዎችን ስያሜ መድቡ፡፡

| | ባህላዊ የምት የሙዚቃ መሣሪያዎች | ባህላዊ የትንፋሽ የሙዚቃ መሣሪያዎች | ባህላዊ የክር የሙዚቃ መሣሪያዎች |
|---|---|---|---|
| ምሳሌ፡- | ነጋሪት | ዋሽንት | በገና |

### መፃፍ

ለጥያቄዎቹ ትክክለኛውን መልሶች ፃፉ፡፡

1. የክር ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያዎችን ለማዘጋጀት ምን ምን ነገሮች ያስፈልጋሉ?
2. ደስ ያላችሁን አንድ ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያ ሥዕል ሳሉ፡፡

## 3ኛ ቀን

### ማዳመጥ

## ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያዎችና የሚሠሩባቸው ቁሶች

### ቃላት

በምሳሌው መሠረት ቃላቱን መድቡ::

| | | |
|---|---|---|
| ነጋሪት | ደወል | ቃጭል |
| ከበሮ | አታሞ | ፅናፅል |

| | ከቆዳ የሚሠሩ | ከብረት የሚሠሩ |
|---|---|---|
| ምሳሌ፡- | ከበሮ | ቃጭል |

### ማጣመር

በምሳሌው መሰረት አጣምራችሁ አንብቡ::

ምሳሌ፡- ቆዳ - ዎች → ቆዳዎች

1. ቀዳዳ - ዎች
2. ጣውላ - ዎች

### ግለንባብ

## የማሲንቆ አዘገጃጀት



ማሲንቆ ከክር ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያዎች መካከል አንዱ ነው:: ማሲንቆ ለማዘጋጀት ብዙ የፈረስ ጭራዎች አንድ ላይ ይሸረባሉ:: ከዚያ በኋላ ሣጥን መሰል ነገር ከጣውላ ይዘጋጃል፤ ድምፁንም ለማጉላት በፍየል ቆዳ ይሸፈናል:: በተጨማሪም በሳጥኑ በአንደኛው ማዕዘን ውስጥ

ቁልቁል አንድ ቋሚ እንጨት ይገባል። በቋሚው እንጨት ላይ የፈረስ ጭራው ይወጠራል። ሌላ ደጋን የመሰለ እንጨትም ይዘጋጃል። በዚህ እንጨት ላይ የፈረስ ጭራ ይወጠራል።

⋆⋆⋆"የፈረሱ ጭራ ለምን የሚያገለግል ይመስላችኋል?"⋆⋆⋆

ሁለቱን የተወጠሩ የፈረስ ጭራዎች ርስበርስ በመገዝገዝ ድምፅ እንዲወጣ ይደረጋል።

## 4ኛ ቀን

## አንብቦ መረዳት

**ለጥያቄዎቹ በምንባቡ መሠረት መልስ ፃፉ።**

1. ማሲንቆ ምን ዓይነት መሣሪያ ነው?
2. የፈረስ ጭራ ለምን ያገለግላል?
3. የፍየል ቆዳ ለምን ያገለግላል?

## ቃላት

**በምሳሌው መሠረት ከ"ለ" ወደ"ሀ" አዛምዱ።**

| | "ሀ" | "ለ" |
|---|---|---|
| ሠ | 1. ክራር | ሀ. ይመታል |
| | 2. ዋሽንት | ለ. ይጎሰማል |
| | 3. ደወል | ሐ. ይነፋል |
| | 4. ማሲንቆ | መ. ይደወላል |
| | 5. ነጋሪት | ሠ. ይደረደራል |

## መፃፍ

ሥርዓተነጥቦቹን በመምረጥ በተገቢ ቦታ ፃፉ፡፡

| ፣ | ፡፡ | ? | ፤ |
|---|---|---|---|

1. ክራር ማሲንቆና በገና የክር የሙዚቃ መሣሪያዎች ናቸው
2. ከበሮ ለመስራት የዋንዛ እንጨት ይጠረባል የከብት ቆዳ ይፋቃል
3. ምን ዓይነት የሙዚቃ መሣሪያ ትወዳላችሁ
4. ከበደ የፈረስ ጭራዎችን ሰበሰበ ሸረበ የጣውላ እንጨትም አዘጋጀ

## 1ኛ ቀን

### ማዳመጥ



**የሠርግ ዘፈኖች**

### ቃላት

ዓረፍተነገር ሥሩ።

1. አሳደጉ  2. አቆላመጡ  3. አደመቁ  4. ዘፈኑ

### ማጣመር

በምሳሌው መሠረት የሌሎችን ቃሎች ቅርፅ ለውጡ።

| ምሳሌ፡- ዘናጭ → ዘናጬ → ዘናጪ | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 1. ዘፋኝ | → | ________ | → | ________ |
| 2. አልቃሽ | → | ________ | → | ________ |
| 3. አዛኝ | → | ________ | → | ________ |

### ግለንባብ

#### ለቀስተኛዋ



ሠፈሩ ያለወትሮው በጩኸት ታምሷል። የአካባቢው ሰዎች ጩኸት ወደሰሙበት አቅጣጫ ይሮጣሉ። እኔም ከሚጮኽበት ቦታ ደረስኩ። አንዲት ትልቅ ሴት መሃል ሆነው ሌሎቹ ደግሞ ዙሪያውን ከበው ያለቅሳሉ። መሃል የቆሙት ለቀስተኛዋም፣

"እጇን አትቅበሩት ይቁም እንደአገዳ፣
ሸኝታበታለች ብዙ ብዙ እንግዳ።
እሷን አትቅበሯት ካንገቷ በላይ፣
ሲወጡ ሲገቡ ልጆቿን እንድታይ"

በማለት በልጃቸው ሞት በሀዘን በተሰበረ መንፈስ ይንሰቀሰቃሉ። በዙሪያው የከበበው ሁሉም ሰው ይጮሃል፤ ያለቅሳል። እኔም ሚጂቿን ባላውቃትም ሁኔታው አስለቀሰኝ።

## 2ኛ ቀን

### አንብቦ መረዳት

ጥያቄዎቹን በምንባቡ መሠረት መልሱ።

1. ሠፈሩ በጩኸት የታመሰው ለምንድን ነው?
2. ሰዎቹስ የሚሮጡት ለምንድን ነው?
3. ተራኪው ያለቀሰው ለምንድን ነው?
4. በእናንተ አካባቢ ሰው ሲሞት በለቅሶ ሥነሥርዓቱ ላይ ምን ምን ይደረጋል?

### ቃላት

ቃላቱን በማመሳሰል አዛምዱ።

| | "ሀ" | "ለ" |
|---|---|---|
| __መ__ | 1. ዙሪያ | ሀ. ትንሽ |
| | 2. ያማረ | ለ. ጭማሪ |
| | 3. ጥቂት | ሐ. ሁልጊዜ |
| | 4. ድጋሚ | መ. ክብ |
| | 5. ዘወትር | ሠ. የተዋበ |

## መፃፍ

መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን በደብተራችሁ ፃፉ፡፡ አስፈላጊ ሥርዓተነጥቦችንም ተጠቀሙ፡፡

# 3ኛ ቀን

## ማዳመጥ

### የሠርግ ዘፈኖች

## ቃላት

በምሳሌው መሠረት ሌሎችን አሚልታችሁ ፃፉ፡፡

ምሳሌ፡- ጉድጓድ ይቆፈራል፡፡

1. ለቅሶ　　2. እርሻ　　3. ጉልጓሎ

## ማጣመር

በብዙ ቁጥር ፃፉ፡፡

ምሳሌ፦ በዓል → በዓሎች

1. ዘፈን　　2. ባህል　　3. ድል　　4. ሰርግ

## ግለንባብ

### ባህላዊ ዘፈኖች



ሰዎች ደስታቸውን ለመግለፅ ባህላዊ ዘፈኖችን ይዘፍናሉ፡፡

⋆⋆⋆“ባህላዊ ዘፈኖች መቼ መቼ ይዘፈናሉ?”⋆⋆⋆

በሠርግ፣ በሥራ፣ በዘመን መለወጫ በዓልና በመሳሰሉት ባህላዊ ዘፈኖችን መዝፈን የተለመደ ነው:: ለምሳሌ በሰርግ ጊዜ ሙሽራዎችንና ወላጆቻቸውን ለማድነቅና ለማሞገስ ይዘፈናል:: በሥራ ጊዜ ደግሞ በተለይ እርሻ ሲታረስ፣ ጉልጓሎ ሲጎለጎል፣ እህል ሲበራይ (ሲወቃ) ወዘተ. አርሶአደሮች ብርታት እንዲያገኙ ይዘፍናሉ:: በበዓላት ቀናትም በዓላቱን የሚገልፁ ባህላዊ ዘፈኖች ይዘፍናሉ:: ባህላዊ ዘፈኖች የህዝብ ቃላዊ ሃብቶች ናቸው:: በአብዛኛው ክንዋኔዎች ሲከናወኑ የክንዋኔዎቹ ማድመቂያዎች ሆነው ያገለግላሉ::

## 4ኛ ቀን

### አንብቦ መረዳት

ጥያቄዎችን በምንባቡ መሠረት መልሱ::

1. ባህላዊ ዘፈኖች የት የት ይዘፈናሉ?
2. አርሶአደሮች በሥራ ወቅት የሚዘፍኑት ለምንድን ነው?
3. ከባህላዊ ዘፈኖች የአንዱን አዝማች ፃፉና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው::

### ቃላት

ክቦቹን በተገቢ ቃላት ሙሉ::




### መፃፍ

መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን በደብተራችሁ ፃፉ::

## 1ኛ ቀን

### ማዳመጥ

**የኢድአልፈጥር በዓል አከባበር**

### ቃላት

ዓረፍተነገር ሥሩ።

1. ገንፎ 2. ዳቦ ቆሎ 3. ፆም 4. ፀሎት 5. ምግብ

### ማጣመር

የተጓደሉ ፊደላትን በማሟላት ቃላት መሥርቱ።

ምሳሌ፦ በ - ል → በዓል

1. ጨ - ረ 2. ዓ - ት 3. ገ - ር 4. አ - በ

### ግለንባብ

## ሐሊማ በአረፋ ዋዜማ



ሐሊማ ጓደኞቿን ይዛ እየሮጠች ወደቤቷ ገባች። የቤቱ ዕቃዎች ሳሎኑን ሞልተውታል። ሐሊማ "አበበ፣ ደብሪቱ እዚህ ቆዩኝ" አለቻቸውና ዕቃዎቹ እንዳይሰበሩ እየተጠነቀቀች መራመድ ጀመረች። "እማዬ! እማዬ!" ብላ ተጣራች። አባቷ ከወደጓሮ ብቅ አሉ። "ምን ሆነሻል?" አሏት።

⋆⋆⋆"አባቷ ሐሊማን፣ "ምን ሆነሻል?" ብለው ሲጠይቋት ምን የምትመልስ ይመስላችኋል?"⋆⋆⋆

“አይ! እኔ ከጓደኞቼ ጋር ላዘጋጅ የነበረውን እቃ ምስቅልቅሉን ስላወጣችሁብኝ ተናድጄ ነው” አለቻቸው። “አይ ልጄ፣ በአረፋ በዓል ሁላችንም ተጋግዘን ቤታችንን ዝግጁ ማድረግ አለብን” አሏት። “እሱማ ትክክል ነህ፤ እኔም እኮ ይህን አስቤ ጓደኞቼን ይዣቸው መጥቻለሁ” አለች ሐሊማ። አባቷም፣ “ጎሽ የእኔ ልጅ! መተጋገዝ እንደዚህ ነው፤ አንቺ ደግሞ የእነሱ በዓላት ገና፣ ጥምቀትና ፋሲካ ሲከበሩ በሥራ ታግዣቸዋለሽ” አሏት።

## 2ኛ ቀን

## አንብቦ መረዳት

ጥያቄዎችን በምንባቡ መሠረት መልሱ።

1. እነሐሊማ የሚያከብሩት በዓል ምን በመባል ይታወቃል?
2. ሐሊማ የተናደደችው ለምንድን ነው?
3. የሐሊማ ጓደኞች እነማን ናቸው?
4. የእነደብሪቱ በዓላት ምን ምን በመባል ይታወቃሉ?

## ቃላት

በነጠላ ቁጥር ፃፉ።

ምሳሌ፦ ጌጦች → ጌጥ

1. ሴቶች  2. አማኞች  3. ታቦቶች  4. ገጠሮች

## መፃፍ

በእስልምና ኃይማኖት በዓላት የሚዘጋጁ የምግብና የመጠጥ ዓይነቶችን ፃፉ።

| ምግብ | መጠጥ |
|---|---|
| ዶሮ ወጥ | አብሽ |

## 3ኛ ቀን

### ማዳመጥ

**የኢድአልፈጥር በዓል አከባበር**

### ቃላት

**ዓረፍተነገር ሥሩ።**

1. ጎረቤት 2. ፍራፍሬ 3. ሶላት 4. መዝናናት

### ማጣመር

**ቃላትን ወደብዙ ቁጥር ለውጡ።**

1. ጎረቤት → ጎረቤቶች

1. ካህን 2. ቄስ 3. ተከታይ 4. ሼህ

### ግለንባብ

## የጥምቀት በዓል አከባበር

የጥምቀት በዓል በየዓመቱ ጥር አሥራአንድ ቀን በደመቀ ሁኔታ ይከበራል።

***"በአዲስ አበባ ከተማ የሚኖሩ አብዛኛዎቹ ሴቶች ምን አይነት ልብስ ይለብሳሉ?"***

በአዲስ አበባ ከተማ የሚኖሩ አብዛኛዎቹ ሴቶች ፅአዳ የአገር ባህል ቀሚስ ለብሰው ያጌጣሉ። በከተራ (በዋዜማው ዕለት) የየቤተክርስቲያናቱ ታቦቶች ታጅበው ወደ ጃን ሜዳና ወደተዘጋጀላቸው ሌሎች ማደሪያ ስፍራዎች ይሄዳሉ። ታቦቶቹ በአማኞች፣ በካህናትና በቀሳውስት ይታጀባሉ። ከዚያ በኋላ ሌሊቱን በሙሉ ፀሎት ሲደረግ ያድራል። ሲነጋ በጧት አማኞች ይጠመቃሉ። ከዚያም ረፋድ ሲል ካህናት እያሸበሸቡ፣ መዘምራን እየዘመሩ፣ ወጣቶች እየጨፈሩ ታቦታቱን አጅበው ወደየቤተክርስቲያኖቻቸው ያስገባሉ።

## 4ኛ ቀን

### አንብቦ መረዳት


ጥያቄዎችን በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

1. የከተራ (የጥምቀት ዋዜማ) እለት ታቦቶች ወደየት ይሄዳሉ?
2. በጥምቀት በዓል በአዲስ አበባ ከተማ የሚኖሩ አብዛኞዎቹ ሴቶች በምን አይነት ልብስ ያጌጣሉ?
3. የጥምቀት በዓል ሲከበር አይታችሁ ታውቃላችሁ?

   ምን ምን ነገሮችን አይታችኋል?

### ቃላት

ሳጥኖቹን በተገቢ ቃላት አሟሉ።




### መፃፍ

የድርጊት ቅደምተከተሎችን በምንባቡ መሠረት ፃፉ።

የጥምቀት በዓል አከባበር

መጀመሪያ፡- ታቦታት ወደ ጃን ሜዳ ወይም ወደ ተዘጋጀላቸው ሌሎች ማደሪያ ስፍራዎች ይወርዳሉ።

በመቀጠል፡- የእምነቱ ተከታዮች ሲፀልዩ ያድራሉ።

ከዚያ በኋላ፡- ______________________________ ።

በመቀጠል፡- ______________________________ ።

በመጨረሻ፡- ______________________________ ።

## 1ኛ ቀን



### ማዳመጥ

የአርበኞች ተጋድሎ

### ቃላት

ዓረፍተነገር ሥሩ::

1. ዘመቱ 2. ተዋጉ 3. ተፋለሙ 4. ተሸነፉ 5. ነፃ አወጡ

### ማጣመር

በምሳሌው መሠረት ሌሎች ቃላት መስርቱ::

ሠራተኛ → ሠራተኞች

1. አርበኛ 2. ሰልፈኛ 3. ፈረሰኛ

### ግለንባብ

ግንቦት 20




እለቱ የግንቦት 20 በዓል የሚከበርበት ነው:: ትምህርትቤቱ በተለያዩ ሰንደቅ ዓላማዎች አሸብርቋል:: ተማሪዎች የደንብ ልብሳቸውን ለብሰዋል:: መፈክሮችንና ትንንሽ ሰንደቅ ዓላማዎችን ይዘዋል:: መምህሮችም ተማሪዎቻቸውን ለማሰለፍ ላይታች ይላሉ:: ተማሪዎቹ ተሰለፉ::

⋆⋆⋆"ተማሪዎች ከተሰለፉ በኋላ ምን የሚያደርጉ ይመስላችኋል?"⋆⋆⋆

መዝሙራቸውንም እየዘመሩ ወደ መስቀል አደባባይ ተመሙ:: "ነፃነት ያኮራል ሃገር ያስከብራል፤" የሚለው የመዝሙራቸው አዝማች ጎልቶ ይሰማል:: መስቀል አደባባይ ደረሱ:: በአራቱ ማዕዘናት ህዝቡ ወደ አደባባዩ ነጎደ፤ ፈረሰኞችም ፈረሶቻቸውን አሳምረውና አስጊጠው እየጋለቡ ለበዓሉ ድምቀት ሰጡት::

## 2ኛ ቀን

### አንብቦ መረዳት

ጥያቄዎችን በምንባቡ መሠረት መልሱ::

1. ትምህርት ቤቱ ያሸበረቀው ለምንድን ነው?
2. የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ምን ምን ዓይነት ቀለማት አሉት?
3. በእናንተ ትምህርትቤት የድል በዓላትን እንዴት ታከብራላችሁ?

### ቃላት

ዓረፍተነገር ሥሩ::

1. ሰልፍ 2. መዝሙር 3. በዓል

### መፃፍ

ወደሰልፍ ስትሄዱ ምን ምን ነገሮችን ትይዛላችሁ? በቡድን ተወያዩና ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ::

## 3ኛ ቀን

### ማዳመጥ

**የአርበኞች ተጋድሎ**

### ቃላት

የኢትዮጵያ ብሄራዊ በዓሎችን ዘርዝራችሁ ፃፉ።

ብሔራዊ በዓሎች

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | | |

### ማጣመር

በአንስታይና በብዙ ቁጥር ፃፉ።

| ተባዕታይ | አንስታይ | ብዙ |
|---|---|---|
| አሽነፈ | __________ | __________ |
| ተዋጋ | __________ | __________ |
| መራ | __________ | __________ |
| ወረረ | __________ | __________ |

### ግለንባብ

## ህዝባዊ በዓላት

በኢትዮጵያ ብዙ ህዝባዊ በዓላት አሉ። እነዚህ በዓላት ብሔራዊ በዓላት ሊሆኑ ይችላሉ። በዓመት አንድ ጊዜ ይከበራሉ።

⋆⋆⋆"የአድዋ ድል በዓል መቼ ይከበራል?"⋆⋆⋆

የአድዋ ድል በዓል የካቲት 23 ቀን ይከበራል:: የነፃነት ቀን ደግሞ ሚያዝያ 27 ቀን ይከበራል:: ሌላው የህዝብ በዓል ሚያዝያ 23 የሚከበረው የሠራተኞች ቀን ነው:: በተጨማሪም ግንቦት 20 ቀን ደርግ ከስልጣን የወረደበት ሲሆን፣ መስከረም 1 ቀን ደግሞ የዘመን መለወጫ በዓል ነው:: ሁሉም በዓላት በሚከበሩበት ዕለት መሥሪያ ቤቶች ተዘግተው ይውላሉ::

## 4ኛ ቀን

### አንብቦ መረዳት

ጥያቄዎችን በምንባቡ መሠረት መልሱ::

1. ብሔራዊ በዓላት የምንላቸውን ፃፉ?
2. የግንቦት 20 በዓል የሚከበረው ለምንድን ነው?
3. የነፃነት ቀን በዓል መቼ ይከበራል?

### ቃላት

ዓረፍተነገር ሥሩ::

1. ዘመተ 2. ተዋጋ 3. አሸነፈ 4. ተመለሰ 5. ወረረ

### መፃፍ

ጥያቄዎችን በጽሑፍ መልሱ::

1. ከምታውቋቸው መፈክሮች መካከል ሁለቱን ፃፉ::
2. ከምታውቋቸው የድል መዝሙሮች መካከል የአንዱን አዝማች ጽፋችሁ አንብቡ::

## 1ኛ ቀን

### ማዳመጥ



**የፋሲካ በዓል**

### ቃላት

ዓረፍተነገር ሥሩ።

1. ባቄላ  2. ጉልባን  3. ቁርጥ  4. ክትፎ

### መነጠል

በነጠላ ቁጥር ፃፉ።

1. መጠጦች → መጠጥ
2. ቅመሞች → __________
3. ዘመዶች → __________
4. ወዳጆች → __________

### ግለንባብ

**"የፈሰሰ ውኃ..."**

የዶሮ ወጡና የበጉ ሥጋ ጥብስ ሽታ ሆድን ይበረብራል። አይብ፣ እርጎና በቅቤ የረሰረሰ ክትፎ ተደርድሯል። ጠላውና ጠጁ በጠርሙስና በብርሌ ተንቆርቁሮ ቀርቧል። ወይዘሮ ዘርፌ እንግዶቻቸው ዘግይተውባቸው ወጣ ገባ ይላሉ። ድንገት ከወደኋላቸው የኳኳታ ድምፅ ሰሙ።



***"ወይዘሮ ዘርፌ የሰሙት የኳኳታ ድምፅ ምን ይሆናል ብላችሁ ታስባላችሁ?"***

አንድ ድመት እመር ብላ ባጠገባቸው አለፈች። ዞር ሲሉ ልጃቸው ሰይፉ ዱላ ይዞ ሲሮጥ ተጋጨ። "ምንድን ነው ጉዱ?" አሉ ወይዘሮ ዘርፌ። "እማዬ እይው እስኪ!" ብሎ አሳያቸው። በጠረጴዛ ላይ ያለው እርጎ ተደፍቷል። "በል ልጄ የፈሰሰ ውኃ አይታፈስም፤ ሌላ እናቀርባለን" አሉትና ተያይዘው ወደጓዳ ገቡ።

## 2ኛ ቀን

### አንብቦ መረዳት

ለጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት መልስ ስጡ።

1. ከተዘጋጁት ምግቦች ውስጥ የተደፋው ምንድን ነው?
2. ወይዘሮ ዘርፌ ወጣገባ የሚሉት ለምንድን ነው?
3. እናንተ ሰይፉን ብትሆኑ ምን ታደርጉ ነበር?
4. "የፈሰሰ ውኃ አይታፈስም" ማለት ምን ማለት ይመስላችኋል?


### ቃላት

ዓረፍተነገር ሥሩ።

1. ጠላ   2. ጠጅ   3. ቅቤ   4. እርጎ

### መፃፍ

ሳጥኖችን በምሳሌው መሠረት አሟሉ።




## 3ኛ ቀን

### ማዳመጥ

የፋሲካ በዓል

### ቃላት

የወጥ ዓይነቶችን በክቦቹ ውስጥ ዘርዝሩ።




### ማጣመር

ፊደሉንና ቃላቱን በማጣመር ቃላት መስርቱ።

ምሳሌ፦ ተ _ ለቀቀ → ተለቀቀ

ተ _ በላ　　ተ _ ገደፈ　　ተ _ ጠጣ

### ግለንባብ

#### የዶሮ ወጥ አሠራር



ከበዓላት ምግቦች አንዱ የዶሮ ወጥ ነው። የዶሮ ወጥ አሰራር የራሱ ሂደት አለው። በመጀመሪያ ዶሮ ያስፈልጋል። ከዚያ በኋላ ውሃ ይፈላል። ዶሮው በሰላ ቢላዋ ይታረዳል። ትልልቅ ላባዎች ይነጩና የቀሩት ላባዎች ከቆዳው እንዲላቀቁ የፈላ ውሃ ይጨመርበታል። ጥቂት ቆይቶ ላባውን ከቆዳው በመንጨት እንዲለቅ ይደረጋል።

★★★"በዶሮ ወጥ አሠራር ሂደት የዶሮው ላባ ከቆዳው ላይ በመንጨት ከተላቀቀ በኋላ ምን ይደረጋል?"★★★

ከዚያም በቀሰም ይነፋና ወረቀት በማቀጣጠል ይለበለባል። ከዚያ በኋላ በደንብ ይታጠብና ይበለታል። የተበለተው የዶሮ ሥጋ በሎሚና በጨው ለጥቂት ጊዜ ይዘፈዘፋል። እንደገና ሙልጭ ተደርጎ በደንብ

ይታጠባል:: የተከተፈው ሽንኩርት ይጣድና ይበስላል:: ዘይት፣ በርበሬ ይገባበታል:: በደንብ ከተቁላላ በኋላ የዶሮው ሥጋ ተጨምሮ ይበስላል:: ከዚያም ቅቤ፣ ቅመማቅመምና ተቀቅለው የተላጡ እንቁላሎችን በመጨመርና የጨውንም ልክ በማስተካከል ይወጣል::

## 4ኛ ቀን

### አንብቦ መረዳት

ለጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልስ ስጡ::

1. ላባው ከተነጨ በኋላ ዶሮው ወረቀት በማቀጣጠል የሚለበለበው ለምንድን ነው?
2. ቀጥሎ የቀረበውን የዶሮ ወጥ አሠራር ቅደምተከተል አስተካክላችሁ ፃፉ::

| | | | |
|---|---|---|---|
| ይሠራል | ይለበለባል | ይታረዳል | ይገዛል |
| ይጨመራል | ይበለታል | ይዘፈዘፋል | |

### ቃላት

የመጠጥ ዓይነቶችን በሳጥኖቹ ውስጥ ፃፉ::

መጠጦች

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ጠላ | | | | |

### መፃፍ

ሥርዓተነጥቦችን በተገቢ ቦታ ፃፉ::

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፣ | ? | ፤ | :: |

1. ለዓመት በዓል ዶሮ ይገዛል ይታረድና ይሠራል
2. ገበያ ሄጄ ሽንኩርት ዘይትና በርበሬ ገዛሁ
3. ዶሮ ወጥ ለመሥራት ምን ምን ነገሮች ያስፈልጋሉ

## 1ኛ ቀን

## ማዳመጥ



ቀረርቶና ፉከራ

## ቃላት

ዓረፍተነገር ሥሩ፡፡

ምሳሌ፡- ስሜት → ቃላዊ ሀብቶች ስሜትን ይቀሰቅሳሉ፡፡

1. ቀረርቶ 2. ፉከራ 3. ዜማ 4. ግጥም

## ማጣመር

"አስ-" የሚለውን ቅጥያ ከቃላቱ አጣምራችሁ ፃፉ፡፡

ምሳሌ፡- አስ + ጨነቀ → አስጨነቀ

1. አስ + ተማረ
2. አስ + በጠረ
3. አስ + ፎከረ
4. አስ + ለበሰ

## ግለንባብ

### እነአብርሃም በቡሄ በዓል



የቡሄ በዓል የሚከበርበት እለት ነበር፡፡ እነአብርሃም፤

"ሆያ ሆዬ፤ ሆያ ሆዬ
የእኔማ አባት የሰጡኝ ሙክት
ከግንባሩ ላይ አለው ምልክት፡፡"

የሚሉትንና ሌሎችንም ግጥሞች እየገጠሙ ሲጨፍሩ አመሹ:: የሰፈር ሰዎችም እየመረቁ ዳቦ፣ ብር፣ ሳንቲም ሰጧቸው:: ጓደኛቸው ግን አልነበረም:: ወደቤቱ ሄዱ:: “ምንሆነህ ነው የቀረኸው?” አሉት:: “ምን ለብሼ ልውጣ?” አላቸው ፤ እንባ እየተናነቀው:: እነአብርሃምም ተመካከሩና ባገኙት ገንዘብ በማግስቱ ልብስ ገዙለት:: ጓደኛቸውም አቅፎ ሳማቸው::

## 2ኛ ቀን

### አንብቦ መረዳት

ጥያቄዎችን በምንባቡ መሠረት መልሱ::

1. ታሪኩ ስለእነማን ይናገራል?
2. እነአብርሃም ለጓደኛቸው ምን አደረጉለት?
3. የእነአብርሃም ጓደኛ ምን ዓይነት ኑሮ የሚኖር ይመስላችኋል?

### ቃላት

ቃላትን ከአባባላቸው ጋር አዛምዱ::

| “ሀ” | “ለ” |
|---|---|
| 1. ዘፈን | ሀ. ይወረዳል |
| 2. ቀረርቶ | ለ. ይሸለላል |
| 3. ፉከራ | ሐ. ይጨፈራል |
| 4. ሽለላ | መ. ይቅራራል |
| 5. እስክስታ | ሠ. ይፎከራል |
| 6. ጭፈራ | ረ. ይዘፈናል |

### መፃፍ

ዓረፍተነገር ሥሩ::

1. ጨፈረ 2. ሰጠ 3. መረቀ 4. መከረ

## 3ኛ ቀን

### ማዳመጥ

**ቀረርቶና ፉከራ**

ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጡ።

1. ቃላዊ ሃብቶች የምንላቸው ምን ምን ናቸው?
2. ሰዎች ሲያቅራሩ ምን ዓይነት እንቅስቃሴዎችን ያደርጋሉ?
3. ሰዎች ሲፎክሩስ በምን ዓይነት እንቅስቃሴ ነው?
4. የፉከራና የቀረርቶ ዜማዎችን ከእንቅስቃሴ ጋር በክፍል ውስጥ አሳዩ።

### ማጣመር

ወደብዙ ቁጥር ለውጡ።

ምሳሌ 1፦ ግጥም → ግጥሞች

1. ክምር → __________ 3. ምልክት → __________
2. ሙክት → __________ 4. አባት → __________

ምሳሌ 2፦ ፉከራ → ፉከራዎች

1. አውድማ → __________ 3. እርሻ → __________
2. አበጣሪ → __________ 4. ቆፋሪ → __________

### ግለንባብ

## እስክስታ



እስክስታ ባህላዊ የጭፈራ አይነት ነው። በተለይም በአማራ ክልል የተለመደ ውዝዋዜ ነው። ሰዎች ባህላዊ ዘፈኖችን ሲዘፍኑ ወገባቸውን በነጠላ ሸብ ያደርጋሉ። ትከሻቸውን፣ ወገባቸውንና አንገታቸውን በማንቀሳቀስ እስክስታ ይወርዳሉ። የእስክስታ አወራረዱ እንደየአካባቢው ይለያያል።

***"የየት አካባቢ እስክስታ ታውቃላችሁ?"***

የጎንደር፣ የጐጃም፣ የምንጃር፣ የወሎ እስክስታ በመባልም ይገለፃል፡፡ በሠርግ ቦታና በበዓላት ጊዜ የተለመደ ነው፡፡ ባህላዊ ውዝዋዜዎች ሁሉ በእስክስታ የታጀቡ ናቸው፡፡ ስለዚህ እስክስታ ሰውነትንና አእምሮን ዘና ያደርጋል፡፡ የአካል ጥንካሬንም ይሰጣል፡፡

## 4ኛ ቀን

### አንብቦ መረዳት

ለጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ በቃላችሁ ስጡ፡፡

1. የምንባቡን የመጀመሪያ ዓረፍተነገር ለመምህራችሁ ንገሩ፡፡
2. ሰዎች እስክስታ ሲወርዱ ወገባቸውን በምን ሸብ ያደርጋሉ?
3. ባህላዊ ውዝዋዜዎች በምን የታጀቡ ናቸው?
4. እስክስታ ከመዝናናት ሌላ ምን ጥቅም ይሰጣል?
5. ሌሎች የምታውቋቸውን ባህላዊ ውዝዋዜዎች ግለፁ፡፡

### ቃላት

ዓረፍተነገር ሥሩ፡፡

1. ተወዛወዘ 2. ጨፈረች 3. አበጠረ 4. ፎከረች

### መፃፍ

በምሳሌው መሠረት አሟልታችሁ ፃፉ፡፡

